# ቅንነትና ቅን ልቦና በኢትዮጵያ ፖለቲካ ዉስጥ

በሸንቁጥ አየለ/shenkutayele@yahoo.com/

አንድ የኢትዮጵያ ፖለቲከኛ በቅን ልቦና ለሀገሬ ይብጃታል ብዬ ይህን ተናገርኩ ወይም ይህን አደረግሁ ቢል የኢትዮጵያን ፖለቲካ ከሚከታተልዉ ኢትዮጵያዊ ዉስጥ ስንቱ በቅን ልቦና እዉነት ነው ብሎ ይቀበለዋል? የሚል ጥያቄ ቢነሳ እያንዳንዱ ሰዉ ድብልቅልቁ የወጣ መልስ እንደሚሰጥ ይጠበቃል። ኢትዮጵያ ከገባችበት የከፉ ቅርቃሮች ሁሉ የከፋዉ ይሄዉ በቅን ልቦና አንድ ሰው አንድን ድርጊት ሊከዉን ይችላል ብሎ ለማሰብ የሚያስችለዉ መደላድል በኢትዮጵያ ፖለቲካ ዉስጥ ከተናጋሪዉም ሆነ ከአድማጩ በኩል የመጥፋቱ ጉዳይ ይመስላል። በኢትዮጵያ የፖለቲካ ቀለበታማ አዙሪት ዉስጥ መላእክት እንኳዋን በቅን ልቦና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን ቢናገሩ በቅን ልቦና የሚያምናቸውና የሚከተላቸዉ ወገን እንዳይኖር የቅን ልቦናና የሸፍጥ ባህሪ ዋጋቸዉ እስኪቀላቀል እና እስኪምታታ ድረስ ብሎም ሸፍጥ እና ሸፍጠኛ ከአንገቱ ቀና እንዲል የቅን ልቦና ባለቤት ቅን ዜጎች ግን ሁሉን ባለማመን ምንንም በማመን ህላዌ አልቦ ማህበረሰብ ይፍጠር ዘንድ ኢትዮጵያዉያን ፖለቲከኞች የተከተሉት ከእነሱ በተቃራኒ የቆመዉን/ ይቆማል ተብሎ የሚታሰበዉን ወገን/መደብ ሁሉ አጥፍቶ የራስ ወገን/ መደብ ህልዉናን ማስቀጠል/ eliminating the other classes/ የሚለዉ ህሳቤ ቁልፍ ሚና ተጫዉቱዋል።

ይህ ሁሉን በሸፍጥ አጥፍቶ የራስ ወገን/ መደብ ህልዉናን ማስቀጠል የሚለዉ ህሳቤ የመደብ ትግል ሁል ጊዜ የሚደመደመዉ አንደኛዉ ወገን ሙሉ ለሙሉ ሲደመሰስ ነዉ ከሚለዉ ህሳቤ የሚቀዳ ሆኖ በተዋረድም ከለማኘ የአእምሮ ህሳቤ ጋር ተጣበቆና የእነገሌ ህልዉና ካልከሰም የእኛ ህልዉና በኢኮኖሚ፡ በፖለቲካ ፡ በማህበራዊና በሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ሁሉ ላእላይ መዋቀሩ ዉስጥ ሊረጋገጥ አይችልም የሚል ትንታኔን ተንተርሶ የፍልስፍና አድማሱን ያሰፋል። የፍልስፍና አድማሱ ደግሞ የሚሰፋዉ በሸፍጥና በሀሰት ላይ በመንተራስ ይሆናል ማለት ነዉ። በተያያዥነትም በሸፍጥና በሀሰት ስሌት የሚመራ ፖለቲከኛ እዉነትን ፡ ትብብርን ፡ የጋራ ህላዌን ብሎማ ዘላቂ ሁል አቀፍ ብልጽግናን መሰረት ያደረገ ረዥም መንገድን ለመራመድ የሚችል ንድፈ ሀሳብን ለመቅረጽ ይቅርና በፍላጎት ደረጃ ፊቱን ወደ እነዚህ ጉዳዮች ለማዞር አይፈልግም።

የመደብ ትንታኔ ያሳበዳቸዉ አቢዮተኞች፡ የብሄር ጉዳይ የሚያቃዣቸዉ ፖለቲከኞች፡ የግል ቂምና ዝና የሚያናዉዛቸዉ ፖለቲከኞች በግራና በቀኝ ተፋጠዉ ቢቆሙም የቅን ልቦናና ቅንነት ጉዳይ ከሁሉም ዘንድ የራቀች ሆናለች። የቅን ልቦናና ቅንነት ጉዳይን የሚያጠፋዉ ህሳቤም የመደብ ትንታኔ ያሳበዳቸዉ አቢዮተኞችም፡ የብሄር ጉዳይ የሚያቃዣቸዉ ፖለቲከኞችም፡ የግል ቂምና ዝና የሚያናዉዛቸዉ ፖለቲከኞች አንድ የጋራ መሰረታዊ የአስተሳሰብ ቅኝት አላቸዉ። ይህም ከእነሱ በተቃራኒ የቆመዉን/ ይቆማል ተብሎ የሚታሰበዉን ወገን ሁሉ አጥፍቶ የራስ ወገን/ መደብ ህልዉናን ማስቀጠል/ eliminating the other classes/ የሚለዉን ፖለቲካዊ ህሳቤ እንደ ግልና አዳኝ ፖለቲካዊ እምነታቸዉና ሀይማኖታቸዉ የተቀበሉት በመሆናቸዉ ነው። ይህም ፖለቲካዊ እምነትና ሀይማኖት የመጨረሻ ዉጤቱ የራስና የግል መደብ/ወገን ህልዉና ብሎም የበላይነት በሚለዉ ጥልቅ ግን እጅግ ጠባብና ከብረት የጠነከረ መርህ ላይ የቆመ በመሆኑ መቻቻል፡ በቅንነትና በቅን ልቦና ላይ የተመሰረተ የጋራ ህልዉና ብሎም ዘላቂነት ያለዉ ሁል አቀፍ ማህበረሰባዊ ብልጽግና የሚለዉ ታሳቢ ህሊናና ልቦናቸዉን ሊገዛዉ አይችልም።

እንዴዉም በቅንነትና በቅን ልቦና የሚለዉ ህሳቤ ሲነሳ የሚመጣባቸዉ የመጀምሪያዉ ታሳቢ ከዚህ ህሳቤ ጀርባ ምን የተጠነጠነ ደባ ይኖር ይሆን የሚለዉ ስሌት ነዉ። እንዲያዉም በኢትዮጵያ ፖለቲካ በቅንነትና በቅን ልቦና ይከወናል በሎ ማሰብ የሞኞችና የጅሎች ህሳቤ ነዉ የሚል ድምዳሜ ከፖለቲከኞቻችን ህሊና የሚፈልቅ እስኪመስል በግራም በቅኝም የቅንነትና ቅን ልቦና ጉዳይ ተረት ተረት ሆናለች። በተያያዥነትም አንድ የኢትዮጵያ ፖለቲከኛ በቅን ልቦና ለህገሬ ይብጃታል ብዬ ይህን ተናገርኩ ወይም ይህን አደረግሁ ቢል የኢትዮጵያን ፖለቲካ ከሚከታተልዉ ኢትዮጵያዊ ዉስጥ ስንቱ በቅን ልቦና እዉነት ነው ብሎ ይቀበለዋል? የሚል ጥያቄ ሲነሳ የህዝቡ መልስ ፈገግታ ብቻ ሆኖ ያርፋል። እንዴት እንዲህ አይነት ጥያቄ ይጠየቃል ለማለት ወይም ምነዉ ብትተወኝ ለማለት።

*ሆኖም ቅንነትና ቅን ልቦና በኢትዮጵያ ፖለቲካ ዉስጥ መስፈን ሳይችሉ ማህበረሰቡም ሀገራዊ ፖለቲካ በቅንነትና ቅን ልቦና ይከወናል ብሎ ካላመነ በህግና ስርአት የቆመ ዘላቂነት ያልዉ ብልጽግና እየተነገረ ብቻ የሚቀር ተረት ተረት ከመሆነም በባሰ ሁኔታ ምናልባትም የጋራ ህልዉናን ሊዉጥ የሚችል በአለመተማምን ላይ የተመሰረተ ሁሉን አጥፊ የሆነ ፖለቲካዊ ቀመር ገፍቶ ሊመጣ ስለሚችል ከግራም ከቀኝም የቆሙ የኢትዮጵያ ፖለቲከኞች ሁሉ የቅንነትና ቅን ልቦናን ጉዳይ በጥንቃቄ ቢያንሰላስሉት መልካም ነዉ።*

*በፖልቲካ ሂደት ዉስጥ የቅንነትና ቅን ልቦና ጉዳይ ከመንፈሳዊነት ጋር ወይም ሌላዉን መድብ ከመዉደድ ጋር አይገናኝም። የቅንነትና ቅን ልቦና መሰረታዊ ማጥንጠኛዉ ዘላቂነት ያልዉ በህግና ስርአት ላይ በተመሰረት ሁል አቀፍ ማህበረሰባዊ ብልጽግና ሊኖር የሚችለው ፖለቲከኞች ከመደብ መጠፋፋት ህሳቤ ሲወጡ በሎም ሀገሩ የጋራ ነዉ : ሁሉም ወገን በሀገር ጉዳይ የሚያራምደዉ ራእይ ለሀገር የሚበጅ ሊሆን ስለሚችል ሀዝቡ ራሱ የሚጥለዉን ጥሎ የሚያነሳዉን ያንሳ ብሎ በማይናወጥ በቀናነትና በቅን ልቦና ላይ በቆመ ህግና ስርአት : መርህ መታነጽ ሲቻል ብቻ ነዉ። አንዱ ወገን አንዱን መደብ/ወገን አሸንፎ የሌላዉን ህልዉና ደመሰሥኩ በዚህም የራሴን ወገን/መደብ ህልዉና በበላይነት አስቀጥላለሁ የሚለዉን ታሳቢ አንጠልጥሎ ያለ ቅን ልቦና ቅንነት ፖለቲካን መሸረብና መደወር በርግጥም ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን አንዱን ወገን/መደብ በማጥፋት የድል አዋጅን ሊያሳዉጅ ይችል ይሆናል።*

*ሆኖም የድሉ ቆይታ አጭር፡ በስጋት የታጠረ፡ መርዛማ ባህር ዉስጥ በጋራ እንደ መዋኘት ሁሉ መርዛማዉን ዉሃ ሁሉም በጋራ የሚጋትበት በመጨርሻም የሁሉም ዋነተኛ ህልዉና በጋራ የሚከስምምበት ሁኔታ መፈጠሩ አይቀሬ ነዉ። ስለሆነም እያንዳንዱ ለሌላዉ ህልዉና ብሎ ሳይሆን ለራሱ፡ ለልጆቹ፡ ለወገኑ/መደቡ ሲል የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሂደት ከተጣላዉ ቅንነትና ቅን ልቦና በምን መልክ ሊታረቅ እንደሚችል አጥልቆና አጥብቆ ቢሰራ መልካም ነዉ። ቅንነትና ቀና ልቦና በኢትዮጵያ ፖለቲካ ዉስጥ የሚመላለሱ ሀይላትን ሁሉ /ከተቃዋሚ እስከ ገዥ/ የሚመለከት እንጅ ወደ አንዱ ወገን የሚገፋ ጉዳይ አይደለም። ቅንነትንና ቅን ልቦናን በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሂደት ዉስጥ በምን መልክስ ማስፈን ይቻል ይሆን? በሎ ማንሰላሰል የሁሉ ሀላፊነት ነዉና ሁሉ ቀረብ ብሎ ቢመረምረዉ መልካም ብቻ ሳይሆን የሀገሪቱ ህልዉና እራሱ የተንጠለጠለበት ክር መሆኑን ማስተዋል ይቻላል።*

*ስለ ዲሞክራሲ ፡ ስለ ህግና ስርዓት ፡ ስለ ሀገር አንድነት፡ ስለ ብሔሮች እኩልነት ወይም ስለ ልማትና የነገይቱ ኢትዮጵያ ማዉራት ቀላል ነገሮች ናቸዉ። ፖለቲከኞቻችን በቅንነትና በቀና ልቦናን የሀገሪቱን የፖለቲካ ሂደት መከዉን ካልቻሉ ግን ከላይ የተነሱትን ትልልቅ ጽንሰ ሀሳቦች ሁሉም ለነገር ማጣፊቻነት ስለሚጠቀምባቸዉ አንድም ፍሬ የማያፈራ በተቃራኒዉ ግን ሁሉ በሁሉ የሚጠፋፉበት ኩነትንና ኢጋጣሚዎችን በወገቡዋ አዝላ የምትዞር አገር ፡ ህዝቡም በማንም በምንም የማያምን እና የማይታመን ልብን ይዞ የሚንቀሳቀስ ሁሉ መፍሰሻ እንደሌለዉ በይ ዉዳሰኘዉ የሚናዉዝ ይሆናል። እናም ይህን ጊዜ አገር መፍረስ ጀምሮአል ማለት ነዉ። ሀገሪቱን ከዚህ ሁሉ መታደግ የሚችሉት የሀገሪቱ ፖለቲከኞች ብቻ ናቸዉ። እሱም አንድ ነገርን ብቻ በማድረግ። ቅንነትና ቀናነት በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሂደት ዉስጥ መደላድላዊ መሰረት ያለዉ እንዲሆን በማድረግ።*

ከላይ የተነሳዉ *የቅንነትና ቅን ልቦና ጉዳይ ምኝነት ለሚመስላቸዉ ፡ መሰል* ምክርን ሲሰሙ ጆሮአቸዉን ለሚያሳክካቸዉ፤ ምክርን እንቢ ለሚሉ *ፖለቲከኞቻችን* ግን የምትከተለዋን ግጥም ጋብዤ ልለያቸው፡-

**<u>የማይመከር ተመካሪ</u>**

የማይመከር አማካሪ ፣

እዉቀት ማማ ላይ ቆሞ ለሽፍጥ ዘማሪ፤

ብቻ አይደለም ያገር እንቅርት፣

የጥበብ ነቀርሳ ዉግምት፡፡

ዋናዉ ጽልመት የምስለኔነት አራቢ፣

ምክረ ፍርሃት ካባ ደራቢ ፤

እምቢ እያለ የማይመከር ተመካሪ፣

ነፅሮተ ህይወትን በድንቁርና ቀማሪ፣

ዘላለማዊነት ብልጽግናን በግላዊነት አደዋሪ፡፡

---------------------------------------------------------------------------

ሸንቁጥ አየለ፣ ሐምሌ /2004 ዓም ፤ አአ